# የኤርትራ እስር ቤቶች አሳዛኝ ታሪኮች

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

በርካታ ሰዎች በቅርቡ በኤርትራው አምባገነናዊ መንግስት ላይ ከመፈንቅለ መንግስት የማይተናነስ አመፅ ያደረጉት የሀገሪቱ መኮንኖችና ወታደሮች "የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው ምን ይሆን?" በማለት ያብሰለስላሉ– ከአቶ ኢሳያስ ጨካኝ ተፈጥሮአዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪ በመነሳት። እርግጥም ማንኛውም ሰው እንደ ሰብዓዊ ፍጡር የህዝቡን ብሶት በመወከል የዴሞክራሲን ጥያቄዎች አንግበው ለተነሱትና ኋላ ላይም "ጥያቄያችሁ የእኛም ነው" በሚል ሽንገላ ታሳሪ ወደ ማይጠግቡት የሻዕቢያ እስር ቤቶች ለተወረወሩት ለእነዚያ ወታደሮች ማዘኑ ተገቢና ተፈጥሮአዊ ነው።

መቼም ውድ አንባቢዎቼ በቅርቡ "ኦፐሬሽን ፎርቶ እንዴት ከሸፈ፣ አቶ ኢሳያስስ ምን አሉ?" በሚል ርዕስ በአይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ላይ በተስተናገደው ፅሑፌ፣ የዘመቻው ዋነኛ መሪዎች የተባሉት መኮንኖችና ወታደሮች እስር ቤት መግባታቸውን መግለፄን ታስታውሳላችሁ። አዎ! የአስመራው አስተዳደር በሀገሪቱ ውስጥ በይፋ ከሚታወቁት 37 ማጎሪያዎች ውስጥ በአንዱ አሊያም እየበታተነ ወይም እየለየየ ዜጎቹን በሚያሰቃይባቸው የኮንቴይነር እስር ቤቶች እንደዶላቸው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። ራሳቸው አቶ ኢሳያስ አመፁ ከተካሄደ ከሶስት ሳምንታት ዝምታ በኋላ ከሀገራቸው መገናኛ ብዙሃን ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ ይህንኑ አረጋግጠዋልና።

ታዲያ ኤርትራ ውስጥ እስር ቤት ማለት የዘግናኝ ድርጊቶች መፈፀሚያ ስፍራ ነው– በቃ! ተመሳሳይ የማሰቃየትና የቂም በቀል ተግባር የሚከናወንበት ቦታ። እዚያ ቦታ ላይ ማንም ትላንት ስለከወነው ብርቅዬ ተግባር ወሮታው አይነሳም። ትናንት እርሱ ማንም ቢሆን የሚመዘነው በዛሬው እስረኛነቱ ብቻ ነው– ለዚያውም የእስረኝነት ወግ ማዕረግ ሳይኖረው። በኤርትራ እስር ቤቶች ውስጥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ያላቸው ጠባቂዎች ብቻ ናቸው። አዎ!  በሻዕቢያ ዘብጥያ እንዲወርዱ ከተደረጉት 35 የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ውስጥ 15ቱ በህክምና እጦት ፣ በረሃብና በድብደባ ስቃይ እንዲሁም በአካባቢው ባለው ከፍተኛ ሙቀት ህይወታቸው አልፏል፡፡

እስር ቤቶቹ የቀድሞውን የሀገሪቱን ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ መሀመድ ሸሪፎን /ኤርትራ ምክትል ፕሬዚዳንት የሌላት ሀገር መሆኗን ልብ ይሏል/ እንዲሁም ጄኔራል ዕቁባይ ኣብርሃ እና አምስት ጋዜጠኞችን ቅርጥፍ አድርገው በልተዋል። በጣም አሳዛኙ ነገር ግን በኢትዮ-ኤርትራ

ጦርነት ወቅት እ.ኤ.አ በ2000 ኤርትራ በመወከል ከኢትዮጵያ ልዑክ ጋር አልጀርስ ላይ የተፈራረሙት የቀድሞው የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ወልደትንሳይ በደረሰባቸው ዘግናኝ ድብደባ ምክንያት ሁለቱም አይኖቻቸው እንዲጠፉ መደረጉ ነው፡፡ ሌሎች እስረኞችም 24 ሰዓት እጅና እግራቸው በካቴና ተጠፍሮ ዕለተ-ሞታቸውን እየተጠባበቁ መሆናቸውን የዓይን እማኞች ያስረዳሉ። እናም የአመፁ መሪዎችና ወታደሮች ሊደርስባቸው የሚችውን ነገር ለመገመት አይከብድም።

ያም ሆነ ይህ ግን በዛሬው ፅሑፌ የህዝቡን ጥያቄ አንግበው የዴሞክራሲን ፅዋ ለማንሳት በሀገረ-ኤርትራ ውስጥ የሚባትሉ ፋኖዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ የሚወረወሩባቸውን እስር ቤቶች አደገኛና ዘግናኝ መንጋጋዎችን ለውድ አንባቢዎቼ ለማሳየት እሞክራለሁ። የእስር ቤቶቹ ሁኔታም ማንኛውም በአቶ ኢሳያስ ስልጣን የመጣ ወይም የአቶ ኢሳያስን የአፈና ህግ የተፃረረ ሰው የሚያገኘውን ፍዳ የሚያሳይ በመሆኑ፤ ሰሞነኛዎቹ የአመፁ መሪዎችና ተዋናዮች ቀጣይ ዕጣ ፈንታን አመላካች ሊሆን ይችላል ባይ ነኝ። ለማንኛው እስቲ ወደ አቶ ኢሳያስ እስር ቤቶች አሳዛኝ ታሪኮች ልውሰዳችሁ።…

"…ሰውነቱ በደም ተበክሎ፣ ዓይኖቹን ከድኖ ጥርሱን እያንገጫገጨ ያቃስታል፡፡ በታዘዝነው መሰረት ቃሬዛ ላይ አስተኝተነው ከረን ወደሚገኘው ሆስፒታል እየወሰድነው ነው፡፡ ለአፍታ ትክ ብዬ ተመለከትኩት- ፊቱ ገርጥቷል፡፡ በተከፈተበት የተኩስ እሩምታም ሰውነቱ ተበሳስቷል፡፡ በተዓምር ካልሆነ በስተቀር ይተርፋል ብዬ አልገመትኩም፡፡ ግና ምስጋና ለሆስፒታሉ ሃኪሞች ይድረስና ፈጣን ህክምና ተደረገለት፡፡ ጻሩ ግን ተኩሱ በጭካኔ የተሞላ ስለነበር፤ የወጣቱ አንድ ኩላሊት ከጥቅም ውጪ ሆኗል፡፡ አንዱ እግሩም ሽባ የሆነ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ የ24 ዓመቱ የከረን ከተማ ተወላጅ ወጣት ስሙ ኢሳ ሳልህ የሚባል መሆኑን ያወቅኩት፣ ሁለታችንም እጆቻችን የኋሊት ተጠፍረው ወደ ሳዋ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ለስልጠና የተወሰድን ዕለት ነው።እንግዲህ ይታያችሁ! እኔ እንኳን ወታደራዊ ስልጠና ልሰልጥን፣ ይህ በጨቅላነቱ አካለ ጎዶሎ የሆነው ወጣት ግን እንዴት ነው ሊሰለጥን የሚችለው ?– በገዛ ወገን ላይ የሚፈጸም የግፍ ቅጣት ካልሆነ በስተቀር፡፡ …"

የዚህ ትዕይንት የዓይን እማኝ የ51 ዓመት ጎልማሳ ናቸው – አቶ ሙሴ ሓድጉ፡፡ ጎልማሳው ልጃቸው በሻዕቢያ የአፈና ቡድን የት እንደደረሰ ባለማወቃቸው እርሱን ፍለጋ ከእስር ቤት እስር ቤት ሲማስኑ፤ በአቶ ኢሳያስ እስር ቤቶች ያዩትን የስቃይ፣ የእብደትና የሞት አሳዛኝ ታሪኮችን በስደት ከሚገኙበት ኡጋንዳ በአንድ ወቅት "ህይወት በሻዕቢያ አገዛዝ ስር" በሚል ርዕስ እንካችሁ ካሉን ፅሑፍ ቀንጭቤ የወሰድኩት ነው፡፡…

"ኧረ ልጄን ያያችሁ? በማለት እንደ የምዕተ-ዓመቱን የልማት ግብ እንደሚያሳ የጤና ኬላዎች በቅርብ ርቀት በተሰሩት የአስመራው አምባገነን ቡድን አካባቢ በመገኘታቸው ሳቢያ "እዚህ ምን ትሰራለህ?፣ ስለየትኛው ልጅ ነው የምታወራው?" ተብለው "ሓዲሽ መዓስከር" እየተባለ ወደ ሚጠራው እስር ቤት የተወረወሩት አቶ ሙሴ፤ የኤርትራን መንግስት የግፍ አገዛዝ የተቃወሙ አሊያም ወደ ጎረቤት ሀገሮች ለመጥፋት ጥረት የሚያደርጉ ወጣቶች በአቶ ኢሳያስ ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ትዕዛዝ ሆን ተብሎ ህክምና እንዳይሰጣቸው፣ ዘግናኝ ግርፋትና ስቃይ እንዲደርሳባቸው እንዲሁም ቀስ በቀስ እንዲሞቱ እንደሚደረግ ይገልፃሉ፡፡

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኤርትራ መንግስት ከአሸባሪነቱ ባሻገር፤ በራሱ ህዝብ ላይ ከሚፈጽመው ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እንዲቆጠብ በተደጋጋሚ ቢያሳስብም፤ አምባገነኑ የኢሳያስ አፈወርቂ አስተዳደር ግን "ከኛ በላይ ለህዝባችን ልታስቡ አትችሉም" በሚል በተለመደ የማደናገሪያ ሃሳብ የፀረ-ዴሞክራሲያዊነትን አክሊል ደፍቶ በተደጋጋሚ ለማላዘን እየሞከረ ነው፡፡

ታዲያ ይህን የአቶ ኢሳያስን የለየለት ቅጥፈት "ውስጡን ለቄስ" የሚሉት አቶ ሙሴ፣ ራሳቸው ከሁለት ዓመት በላይ ሰለባ የነበሩባቸውን የተለያዩ ከምድር በታች የሚገኙ እስር ቤቶችን ዘግናኝ ድርጊቶች በምሬት እየተንገሸገሹ በሃሳብ ባህር የኋሊት ተጉዘው የበርካታ ኤርትራዊያንን ግፍ የተሞላበት ስቃይና ሞትን ተርከውታል፡፡ እኔም የጎልማሳውን ትርክት ተመርኩዤ በሻዕቢያ እስር ቤቶች ውስጥ የሚከናወኑትን አሳዛኝ ታሪኮች እንዲህ አቀረብኩላችሁ፡፡

### ❖ የበረኸት መንግስተኣብ የወንድም ልጅ …

ውልደቱና ዕድገቱ በኤርትራ ማዕከላዊ ዞን ውስጥ የምትገኘው "ሓዘጋ" መንደር ውስጥ ነው – የ30 ዓመቱ ወጣት ምስግና ተስፉልደት መንግስተኣብ፡፡ እስር ቤት ከመግባቱ በፊት የአዕምሮ ችግር እንደነበረበት የሚታወቀው ይህ ወጣት፣ የታዋቂው የኤርትራው ዘፋኝ የበረከት መንግስተኣብ የወንድም ልጅ ነው፡፡ ዳሩ ግን ምን ያደርጋል?– የአዕምሮ በሽተኛነቱም ሆነ የበረኸት መንግስተኣብ አጎትነት ከሻዕቢያ የስቃይ መንጋጋዎች ሊያስጥሉት አልቻሉም፡፡

የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በስርዓቱ ላይ አንዳች አሉታዊ ተግባር የፈጸመን ሰው ያለምንም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ አንገቱን አንቆ ወደ እስር ቤት የሚወረውር በመሆኑ፤ ልክ በመግቢያችን ላይ እንዳነሳነው የ24 ዓመት ወጣት በሽተኛ እንዲህ አይነቱ ግለሰብ ወደ ሌላ የበቀል ስፍራ ይላካል፡፡ እናም የምስግና ህይወት ከዚህ ነባራዊ "ሻዕቢያዊ ብቀላ" የሚዘል አይሆንም፡፡ የአዕምሮ በሽተኛው ወጣት የእስር ቤት አሳዛኝ ህይወትም እንዲህ ይነበባል፡፡…

…በአንድ ወቅት ከሚኖርበት መንደር በአቶ ኢሳያስ የአፈና ቡድን ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በኃይል ታፍሶ ወደ ሳዋ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ እንዲገባ ተደረገ፡፡ ይሁንና

ወጣቱ የአዕምሮ በሽተኛ መሆኑ በማሰልጠኛ ካምፑ የሀኪሞች ቦርድ በመረጋገጡ፣ በሃኪሞች ብርታት ከሳዋ እንዲወጣ ተደረገ፡፡

በበሽተኛ አዕምሮው ወዴት እንደሚሄድ እንኳን በቅጡ የማያውቀው ምስግና፣ እስከ አቑርዳት ከተማ (ከአስመራ 172 ኪሎ ሜትር ያህል) በአውቶብስ ይጓዛል፡፡ እግሩ እንዳመጣለትም ከአውቶብሱ ወርዶ በእግሩ የኤርትራና የሱዳን የጠረፍ ከተማ የሆነችው "ግርማይካ" አካባቢ ይደርሳል፡፡ በአካባቢው የሚገኙት የአቶ ኢሳያስ የአፈና ቡድን አባላት እያዳፉ በአቅራቢያው ወደሚገኘው "ሐዲሽ መዓስከር" የምድር ውስጥ እስር ቤት ይከቱታል፡፡...እስር ቤት ውስጥ በጠባቂዎች "ከሀገር ልትወጣ ነበር" በሚል ሰበብ በደረሰበት ከፍተኛ ስቃይና ድብደባ ሰውነቱ ዛለ፤ ላዩ ላይ የነበረው ልብስም ተቀዳደደ፤ተቦጫጨቀ፡፡...

...ምስግና በዱላ ብዛት ላዩ ላይ የነተበውን እራፊ ጨርቅ አድርጎ፤ አንገቱን ጉልበቱ ውስጥ ቀብሮ እስር ቤቱ በር አጠገብ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል፡፡ ከምድር በታች በሚገኙ እስር ቤቶች ውስጥ እርሱ የተቀመጠበት ቦታ ቀን ከሆነ በሩ ሲከፈት ብርሃን የሚያገኝ ሲሆን፤ማታ ደግሞ ከአካባቢው በሚመጣ የብርሃን ጭላንጭል ደብዛዛ ብርሃን ያርፍበታል፡፡ የተቀሩት የእስር ቤቱ አካባቢዎች ግን ድቅድቅ ጨለማ የዋጣቸው ይሆናሉ፡፡ እናም ቀን ሲሆን፤ እስረኞቹ በሙሉ ብርሃን ለማየት ወደ በሩ አካበቢ ለመቀመጥ ይሯሯጣሉ– ምስግናን በመግፋት፡፡

አዎ! የአቶ ኢሳያስን የግፍ አገዛዝ በመቃወም በእስር ቤቱ ውስጥ ከታጎሩት ከ80 በላይ ኤርትራውያን የተፈጥሮን ብርሃን እንኳን እንዳያዩ የተፈረደባቸው ናቸው፡፡ እናም የብርሃንን ጭላንጭል ለማየት መሯሯጣቸው የሚገርም አይሆንም፡፡ ይሁንና ከእስረኞቹ መካከል እንዲህ አይነቱን ሁኔታንና የ"ወፌላላ" ግርፋትን ለመርሳት ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 20 የሚገመቱ በርካታ ወጣቶች ምስግናን እየጎተቱ ያሾፉበት ነበር፡፡...በተለይም በረኸት መንግስተኣብ አጎቱ መሆኑን በማወቃቸው የሚከተለውን የበረኸትን ዜማ በአንድነት በመዝፈን ይጎትቱት ገቡ፡፡...

*"ኣብ ክራማት ኣብ ሃጋይ መገሻ፣ ተመሊሰ'ዶ ኩለን ብሓፈሻ" ዜማው ወደ አማርኛ ሲመለስ፤"በክረምትም ይሁን በበጋ ጉዞ ሁላችንም በአንድነት ተመለስን አይደል?"* እንደማለት ነው፡፡ ይህ ዜማ ለአዕምሮ በሽተኛው ምስግና ምንም ትርጉም የሚሰጠው ባይሆንም፣ መጎተቱን ግን አልወደደውም፡፡እናም በድቅድቅ ጨለማው ውስጥ በአቅራቢያው ያገኘውን ጫማ አነሳና ወረወረ፡፡ ...አለመታደል ሆነና ጫማው አቅጣጫውን ስቶ በጉዳዩ ውስጥ የሌሉበትን አዛውንት መታቸው፡፡

ነገሩ "ሆድ ለባሰው፣ ማጭድ አታውሰው" ነውና አዛውንቱ ለጠባቂዎቹ ምስግናን ይከሱታል፡ :.. ጠባቂዎቹ ጉዳዩን ምንም ሳያጣሩ ምስግናን በሰደፍ እያዳፉ ወደ ውጭ ወሰዱት፡፡ የምስግና ኡኡታ በሩቁ ይሰማል፡፡ "አደይ!" (እናቴ!) –ይላል የአዕምሮ በሽተኛው ምስግና፡፡ ቀስ በቀስ ድምጹ

እየደከመና እየራቀ ሄደ፡፡ በመጨረሻም ድምጹ ከነአካቴው ጠፋ፡፡ "አደይ!" (እናቴ!) እያለ ሲጮህ የነበረው ምስኪን፣ ኩርምት ብሎ ወደሚቀመጥበት የእስር ቤቱ በር አጠገብ ዳግም ላይቀመጥ በዚያው ቀረ፡፡...

❖ *የክብሮም ስንብት...*

መረጋጋት የተሳነውና በቋፍ ላይ የሚገኘው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በዜጎቹ ላይ በየዕለቱ የሚያወጣቸውን የአገዳ መመሪያዎችን አላወቀም– የመንደፈራ ከተማው ተማሪ ክብሮም፡፡ እናም የትምህርት ቤት መታወቂያውን ሸሚዙ ኪስ ውስጥ ከትቶ ወደ ተሰነይ ከተማ አባቱን ለመጠየቅ ይጓዛል– ሀገር ሠላም ነው ብሎ፡፡ ምንም እንኳን ከመንደፈራ እስከ ተሰነይ ድረስ ይህ ነው የሚባል ችግር ባያጋጥመውም፣ ተሰነይ መግቢያ ላይ ግን "ከሀገር ሀገር በህገ - ወጥ መንገድ ሲዘዋወር የይለፍ ወረቀት አልያዘም" በሚል በሻዕቢያ የአፈና ቡድን ድብደባ ከተፈጸመበት በኋላ፣ ተሰነይ ከተማ የሚገኘው ወታደራዊ እስር ቤት ውስጥ ታሰረ፡፡ ከዚያም ኤርትራና ሱዳን መካከል ወደሚገኘው "ሓዲሽ መዓስከር" እስር ቤት እንዲዛወር ተደረገ፡፡

የ20 ዓመቱ ክብሮም "ሁሉም ለበጎ ነው" በሚል እሳቤ የእስር ቤቱን ስቃይና መከራ በመቻል ሁሌም ፊቱ ላይ ፈገግታ አይለየውም፡፡ ነጫጭ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገ እስረኞቹን የሚያዝናና ሳቂታ ነው – "ማሽላ እያረረ ይስቃል" እንዲሉት ዓይነት መሆኑ ነው የወጣቱ ነገረ ስራ፡፡ ይሁንና ይህ ለጋ ወጣት በአቶ ኢሳያስ የማሰቃየት መንፈስ እየተመሩ ሌት ተቀን የግርፋት ስቃይ የሚያደርሱበትን ጠባቂዎች ሊቋቋማቸው አልቻለም፡፡ ለእስረኞች በቀን አንዴ የሚሰጠው ሻይና ዳቦም ጥንካሬውን እያመነመነው ሄደ፡፡ በዚህም ምክንያት የጤንነቱን ጉዳይ ከዕለት ወደ ዕለት ማሽቆልቆል ጀመረ፡፡...

...እስር ቤቱ የመጀመሪያ ዕርዳታ ብቻ መስጠት የሚችሉ ሁለት ሣዋ የሰለጠኑ ወጣቶች ብቻ ናቸው ያሉት፡፡ እነርሱም ቢሆኑ በራሳቸው ውሳኔ መስጠት አይችሉም። ወደ ክሊኒክ "ሪፈር" የሚሉት በእስር ቤቱ አዛዦች ይሁንታ ብቻ ናቸው፡፡ አዛዦቹ ደግሞ "እስካሁን ድረስ በህይወት አለ እንዴ?" እያሉ የመሞቻ ጊዜን እንዲያፋጥኑ በአቶ ኢሳያስ የአፈና መዋቅር የተመደቡ በመሆናቸው፣ ማንም እስረኛ በ "ሪፈር" ወደ ክሊኒክ እንዲሄድ አይፈልጉም፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጤንነቱ እያሽቆለቆለ የመጣው ክብሮም፣ በከባድ ትኩሳት መሰቃየት ጀመረ፡፡... ዞር ብሎ ያየው ሰው ግን አልነበረም፡፡ እናም በሦስት እና አራት ቀናት ውስጥ ጤንነቱ በአስገራሚ ሁኔታ አሽቆለቆለ፡፡... ስቃዩን ተቋቁሞ ሳቅ ለማለት ቢሞክርም፣ በየመሃሉ ራሱን ይስታል፡፡ ምንም ዓይነት ህክምና ባለማግኘቱም ራሱን መቆጣጠር ተሳነው። እናም ከአምስትና ከስድስት ቀናት በኋላ ልብሱ ላይ መጸዳዳት ጀመረ፡፡...

…ሁኔታውን የተመለከቱት የሣዋ “ሀኪሞችም”፤ ክብሮምን በራሳቸው ፈቃድ ከምድር ውስጥ እርስ ቤት አውጥተው በር ላይ አስተኙት፡፡… ይሁንና “ወዲ ግራናይት” የሚባለው የጠባቂዎች አለቃ እሳት ለብሶ፤ እሳት ጎርሶ መጣ፡፡ ሀኪሞቹ ላይም የሚበቃውን ያህል ከጮኸባቸው በኋላ፤ “ሀኪሞቹ” እንዲቀጡ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ የእስር ቤቱን ጠባቂዎች በመጥራትም ክብሮምን ወደ ምድር ውስጥ እስር ቤት እንዲመልሱት አዘዘ፡፡ እስረኞቹ “ሀኪሞቹ እዚህ ውስጥ ከተኛ ይሞታል ብለዋል” ቢሉም፤ “ወዲግራናይት” ግን ሊሰማቸው አልፈቀደም፡፡ ይባስ ብሎም “ተውት ይሙት!” አለ፡፡… በማግስቱ ከሰዓት በኋላ ላይም ሳቂታውና እስረኞችን ያጽናና የነበረው ክብሮም፤ ዳግም ላይመለስ አሸለበ – ይስቅላቸው የነበሩትን እስረኞችንና ይህን ዓለም፤ በድብደባ በተከሰተ ህመም ሳቢያ ህክምና ሳያገኝ ቀርቶ ተሰናበታቸው፡፡… ሳቁ ግን ከ51 ዓመቱ ጎልማሳ ከአቶ ሙሴ ሓድጉ ህሊና ዛሬም ድረስ አልጠፋም፡፡

### ❖ *የግንበኛው ተስፋ…*

የሸዊት አባት አቶ ገብረሂወት “ዓሊግደር” እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በአንድ የመንግስት ኮንስትራክሽን ውስጥ በግንበኝነት ይሰራሉ፡፡… ተማሪ ሸዊት የአባቱን ናፍቆት አልቻለም፡፡ እናም ትምህርት ቤት ሲዘጋ ከኤርትራ ደቡባዊ ዞን “መራጉዝ” እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ በመነሳት በተሰነይ አድርጎ ወደ አሊግደር ጉዞውን ይያያዘዋል፡፡ ዕድሜው በሃያዎቹ ውስጥ የሚገመተው ይህ ወጣት፣ ተሰነይ ከተማ መግቢያ ላይ ባለው ከፍተኛ ቁጥጥር “የይለፍ ወረቀት የለህም” ተብሎ በአቅራቢያው በሚገኘው ወታደራዊ እስር ቤት ውስጥ ይወረወራል፡፡ … ከዚያም “ሓዲሽ መዓስከር” ወይም “አደርሰር” እስር ቤት እንዲዛወር ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ቤተሰቦቹ “ሸዊት ከአባቱ ጋር ዓሊግደር ነው ያለው” ብለው ሲገምቱ፣ አባቱ ደግሞ እርሳቸውን እንደሚጎበኛቸው ምንም ዓይነት መረጃ ስላልነበራቸው፤ “ሸዊት ከቤተሰቤ ጋር እቤቱ ነው ያለው” በማለት ያስቡ ነበር– እውነቱ የፋሲካ ዕለት እስኪታወቅ ድረስ፡፡…

…ዕለተ ፋሲካ፡፡ የእየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ። የሸዊት አባት የፋሲካን በዓል ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለማክበር ወደ ቤታቸው ያቀናሉ፡፡… ሸዊት ግን አልነበረም፡፡ በዓሉ ጽልመትን ተላብሶ፤ የዚያን ቤተሰብ ደስታ አጠቆረው፡፡… ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ግንበኛው አቶ ገብረሂወት ልጃቸው ሱዳን ጠረፍ በሚገኝ “ሓዲሽ መዓስከር” በሚባል እስር ቤት ውስጥ መኖሩን አንድ ወዳጃቸው ሹክ ይላቸዋል፡፡ እናም አቶ ገብረሂወት ልጃቸውን ለማግኘት ተስፋን ሰንቀው ጉዟቸውን ወደ ሱዳን ጠረፍ ያደርጋሉ፡፡… እውን ተስፋቸው ውጤት ይኖረው ይሆን?… አብረናቸው እንጓዝ።…

…ከብዙ ወጣ ውረድ በኋላ ግንበኛው አቶ ገብረሂወት "ሓዲሽ መዓስከር" እስር ቤት ይደርሳሉ— ተስፋቸውን እንደሰነቁ፡፡ ችግሩ ግን በሀገረ ኤትራ እስረኛን መጠየቅ "ወንጀል ነው" ተብሎ ስለሚታመን፣ እርሳቸውም በአቶ ኢሳያስ ጋሻ ጃግሬዎች "ወንጀለኛ" ተብለው ወደ እስር ቤት እንዳይወረወሩ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው፡፡ እናም የእስር ቤቱ ግንበኛ የሆነውን አንድ የቀድሞ ወዳጃቸውን በሙያቸው እንዲያስቀጥራቸው ይለምኑታል፡፡… ወዳጃቸውም በጥያቄያቸው ተስማምቶና ለሰውዬው ሃላፊነት እንደሚወስድ ለአሰሪዎቹ ገልፆ አቶ ገብረሂወት የግንበኝነት ሥራቸውን በጠረፋማው እስር ቤት ይጀምራሉ፡፡ጥቂት ና‘ቅፋዎችንም የእርሳቸውን እጅ ለሚጠብቁት የሸዊት ሁለት ታናናሽ እህቶችና ለባለቤታቸው እየላኩ፤ የእስረኞችን መግባትና መውጣት በአይነ-ቁራኛ መከታተል ጀመሩ።

…ከቀኑ ስድስት ሰዓት ገደማ ይሆናል፡፡…ሲሚንቶ በማቡካት ላይ ሳሉ፤ እንደ አጋጣሚ ቀና አሉ። እስረኞች በክፍት ወታደራዊ መኪና ተጭነው ሲሄዱ ይመለከታሉ፡፡ እናም አይናቸው ከሰውነት ተራ የወጣው ልጃቸው ላይ አረፈ፡፡ ልጅም አባቱን ትክ ብሎ ማየት ጀመረ፡፡… አባትየው በደመ-ነፍስ የሲሚንቶ ማቡኪያቸውን ጥለው ሩጫቸውን ወደ ወታደራዊ ተሸከርካሪው አደረጉ፡፡ መቼም የወላጅ አንጀት ነውና "ሸዊት!…ሸዊት!" እያሉ መጣራት ጀመሩ፡፡ … እንዴት እንደሮጡ ሳያውቁት ወታደራዊ ተሸከርካሪው ጋ ደረሱ፡፡

… እጃቸውንም በመዘርጋት የሸዊትን እጅ ለመያዝ ሞከሩ፡፡… ሸዊትም "አባ" እያለ ወደ አባቱ እጅ ተጠጋ፡፡… የእስረኞቹ ጠባቂ ግን አቶ ገብረሂወትን በሰደፍ ግንባራቸውን መታቸው፡፡… ግንበኛው አቶ ገብረሂወት ተንገዳገዱ እንጂ፤ አልወደቁም፡፡ ሚዛናቸውን አስተካክለውም ወደ ተሸከርካሪው ጠጋ ሲሉ ፤ ጥይት የጎረሰው የጠባቂው መሳሪያ "ድው" የሚል ድምጽ አሰማ፡፡… አሁን ግን አቶ ገብረሂወት አልተንገዳገዱም፤ የኋሊት ተዘረሩ እንጂ፡፡… መኪናው በፍጥነት ወደፊት ይገሰግስ ስለነበር፣ የዚህ ጽሑፍ ባለቤት አቶ ሙሴ ሓድጉ፣ አቶ ገብረሂወት ይሙቱ ወይም ይኑሩ እርግጠኛ አለመሆናቸውን ይናገራሉ። ይሁንና የግንበኛው ተስፋ ግን እንዲህ ተጠናቋል፡፡…

ውድ አንባቢዎቼ! እነዚህንና ሌሎች አሳዛኝ ታሪኮችን በአይናቸው የተመለከቱት አቶ ሙሴ ሓድጉ፣ ህይወት በአቶ ኢሳያስ ኢ -ሰብዓዊና ፀረ - ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ውስጥ ባሉት እስር ቤቶች ኤርትራውያን ፍዳቸውን እያዩ በመሆናቸው መላው የሀገሪቱ ህዝብ በዚህ አረመኔያዊ ሥርዓት ላይ የተባበረ ክንዱን እንዲያነሳ ጠይቀዋል። ቀደም ሲል የጠቀስኩት የ24 ዓመቱ ወጣት ኢሳ ሳልህ፤ ሣዋ ውስጥ መሞቱን በምሳሌነት በመግለፅ፡፡

አዎ! ማንም ይሁን ማን የአቶ ኢሳያስ አምባገነናዊ መንግስት ህልውና የሚጋፋ እንዲሁም የሀገሪቱን የአፈና መዋቅሮች የሚተላለፍ ዜጋ ትክክለኛ ቦታው እስር ቤት ውስጥ ነው—ሰብዓዊና

ዴሞክራሲያዊ መብቱ እየተገፈፈ ብሎም በብቀላ ቋያ እሳት እየተለበለበ። እናም አቶ ሙሴ እንዳሉት እንዲህ ዓይነቱን መንግስት ሊሸከም የሚችል ዜጋ በሀገረ-ኤርትራ ውስጥ ሊኖር የሚገባ አይመስለኝም። የኤርትራ ውስጣዊ ጉዳይ ያለው በእያንዳንዱ ኤርትራዊያን እጅ ላይ ነውና። አበቃሁ!